MORESH WEGENIE AMARA ORGANIZATION
ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት
P. O. Box 55321, Washington, DC 20040-5321
Tel: (202)-677-0094
Web: http//www.moreshwegenie.org/

ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ታህሳስ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም. ቅፅ፮፣ ቁጥር ፫

# ዐማራን ለማጥፋት የሚጥሩ፣ዐማራ ከመጥፋቱ በፊት ይጠፋሉ!

የተለያዩ ፀረ-ኢትዮጵያ አንድነት የሆኑ ሁሉ፣ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ማጥፋት የሚቻለው፣ዐማራውን ቀድሞ በማጥፋ ነው ብለው ያምናሉ። ለዚህ አባባል ዋቢውም፣ የፋሽስቱ ሞሶሎኒን ወረራን በዓይኑ የተመከለተውና በግብር ያየው፣አዶልፍ ፓርለሳክ የተባለው ፀሐፊ የጻፈውና በተጫኔ ጆብሬ መኮንን፣ «የሃበሻ ጀብዱ» ሲል ወደ አማርኛ የተተረጎመው መጽሐፍ በግልጽ ያስረዳናል።

የፋሽስቱ ውልድ እና የባንዳ ልጆች የሆኑት የትግሬ-ወያኔዎችም ኢትዮጵያን ለማጥፋት አቅደው ሲነሱ፣ በአውራ ጠላትነት ፈርጀው ፈጽሞ ለማጥፋት የተነሱት ዐማራውን መሆኑን፣ በ1968ዓም ያወጡት ፕሮግራማቸው ገጽ 18 ላይ የትግራይ ሕዝብ ጠላት ዐማራው እንደሆነ በይፋ አውጀዋል።

ሞሶሎኒን ዐማራውን ለማጥፋት ላቀደው ዕቅድ ተግባራዊነት ከ800,000 (ከስምንት መቶ ሺ) በላይ ዐማራን «ጋላ-ሲዳማ» እና «ሐረርጌ» ብሎ ከከለለው ክልል የዘር ማጽዳት ወንጀል መፈጸሙን ታሪክ ቁልጭ አድርጎ ይነግረናል። ከማፈናቀሉ ጎን ለጎንም አያሌ ዐማሮች፣ዐማራ በመሆናቸው ብቻ ከመገደል፣ ከመታሰርና ከመጋዝ የተረፉት ለሥራ አጥነትና ለተዋራጅነት ተዳርገው እንደነበር ታሪካችን በግልጽ ያሳያል።

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ የትግሬ-ወያኔ ባለፉት 26 ዓመታት የአገዛዝ ዘመኑ ከአምስት ሚሊዮን ዐማራ በላይ ከኢትዮጵያ ምድረ-ገጽ እንዲጠፋ አድርጓል። በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዐማሮች፣ ዐማራ በመሆናቸው ብቻ፣ ከመሀል፣ ደቡብ፣ ምሥራቅ፣ ምዕራብና ሰሜን ኢትዮጵያ አገራችሁ አይደለም፤ ውጡ ተብለው፣ ሀብት ንብረታቸውን ተነጥቀው፣ከወራሪና ከጠላት በከፋ ሁኔታ እንዲባረሩ መደረጉን የኢትዮጵያ ሕዝብ በትዝብት፣ ዐማራው በእልክና በቁጭት መመልከቱን እናስታውሳለን።

በጥቅሉ ኢትዮጵያን ለመናድ፣ዐማራውን በሁለንተናው መልኩ ከማሳነስ ጎን፣የኢትዮጵያዊነት ምሰሶና ማገር የሆኑትን በቁጥር ከሁሉም በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ ነገዶች ታላቅ የሆኑትን፣የዐማራ የኦሮሞ ነገዶችን «እሳትና ጭድ» በማድረግ የነበራቸውን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ሥነልቦናዊና ደማዊ ግንኙነት አንድነታቸው፣ ከቻሉ መበጣጠስ፣ ካልቻሉ ማላላት፣ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ላቀዱት ዕቅድ ተግባራዊነት ፍቱን መሣሪያ እንደሆነ በማመን፣ሁለቱ ነገዶች በጠላትነት እንዲተያዩ፣ አንዱ የሌላው አጥፊ፣ እንደሆነ ለማሳየት በወታደራዊ ዘመቻ የታገዘ የተቀነባበረ ፕሮፓጋንዳ ከመክፈት ባሻገር፣ ሁሉቱም ነገዶች በታሪካቸው ሊያዩት ቀርቶ፣ ሰምተውት የማያውቁ፣«ዐማራው የኦሮሞን እናቶች ጡት ቆርጧል» የሚል፣«አኖሌ» የተሰኘ፣ የዐማራና የኦሮሞ ትውልዶችን በቋሚ ጠላትነት ፈርጆ የሚያቆም ሀውልት ማቆማቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በግራሞት እያየው መሆኑ ይታወቃል።

በሌላ በኩል የሁሉም ኢትዮጵያዊ ማዕከል፣ የኢትዮጵያዊነት አንድነት፣ ሥልጣኔ፣ ባህል፣ንግድ፣ ኢኮኖሚ፣ ሥነልቦና ትስስር ማብላያ ገበቴ የሆነችውን የአገራችን መዲና አዲስ አበባን፣ ዝቅ ሲልም፣ የኢትዮጵያ ነገሥታት አንዱ የሆነው የዐፄ ዳዊት መናገሻ የነበረችውን የዛሬዋ አዲስ አበባ፣ የዚያን ጊዜዋ «በረራ»ን፣ የአንድ ነገድ ብቸኛ ሀብት ናት፤ የልዩ ጥቅም ተጠቃሚ መሆን ያለበት ያ ነገድ ወይም ኦሮሞ ነው በማለት የሁሉንም ቤት አዲስ አበባን ለኦሮሞ ሰጥቻለሁ ሲል አወጀ። ወያኔ  አዲስ አበባ  የኦሮሞ ሕዝብ ናት፣ በዚህም ነገዱ ወይም አስተዳደሩ ልዩ ጥቅም ይገባዋል ያለው፤ ለኦሮሞ ነገድ ጥቅምና መብት መከበር ተጨንቆ ሳይሆን፣ በአዲስ አበባ ይገባኛል የመብት ጥያቄ፣ ዐማራውና ኦሮሞው ወደ ከፋ ጥል ይገቡልኛል ብሎ ከማሰብ የመነጨ ሤራ መሆኑን ማንም የትግሬ-ወያኔን የትግል ጉዞ የመዘነ ሰው ይስተዋል አይባልም።

ይህ ሤራ ግን እንደ ቀደምቶቹ ሁሉ የሠራ አልሆነም። ለዕቅዱ አለመሥራት ዋናው ምክንያት፣ የዐማራና የኦሮሞ ነገዶች ምሑራን፣ የወያኔ ኅልውና የተመሠረተው በኦሮሞና በዐማራ ነገዶች ፍቺ ላይ መሆኑን ዘግይተው ከመገንዘባቸው በመነጩ ምክንካቶች፣ ወያኔ ላጠመደው የመነጣጠያ ወጥመድ የሁለቱም ነገድ ፖለቲከኞችና አክቲቪስቶች ላለመግባት ብርቱ ጥንቃቄ በማድረጋቸው ነው።

ይህ በትግሬ-ወያኔ ዐማራና ኦሮሞን በአዲስ አበባ ይገባናል የመብት ጥያቄ፣ እንዳለፉት ዕቅዶቻቸው ሁሉ፣ እሳትና ጭድ እናደርጋቸዋለን ብለው አስበው ፣አውጥተው አውርደው፣ ተጨንቀው ያወጡት የሤራ ዕቅድ፣ ከእነርሱ ፍላጎት በተቃራኒ፣ ዐማራና ኦሮሞውን ከማለያየት ይልቅ፣ወደ አባቶቻቸው ወደ ጥንቱ አንድነታቸው እንዲመለሱ አንቂ የመረዋ ደወል ሆናቸው።

ትናንት «ኦሮሞ መገንጠል አለብን»፣ «ዐማራው ቅኝ ገዥ ነው» ይሉ የነበሩ ወገኖች፣ ወደ ዕውነተኛው ኅሊናቸው እንዲመለሱና፣ የሁለቱም ነገዶች ኅልውና ሆነ፣ የኢትዮጵያ አንድነት ሊረጋገጥ የሚችለው፣ የሁለቱ ነገዶች አንድነት ሲጠበቅና ሲረጋገጥ እንደሆነ የአዲስ አበባ የጥቅም ጉዳይ አዋጅ አነቃቸው። ይህን ተከትሎ ዐማራው «የኦሮሞው ደም ደማችን ነው!» ሲል ኦሮሞውም በበኩሉ« የዐማራው ደም ደማችን ነው!» በማለት አዎንታዊ አጸፋውን መመለሱና ይህ ድምፅ አድማስ እስከ አድማስ ማስተጋባት የወያኔን እንደ ድሮው አስፈራርቶ የመግዛት አቅሙን እሳት ውስጥ እንገባ ጅማት የኋሊት አኮማተረው። የሁለቱ ነገዶች ኅብረትና አንድነት ለኢትዮጵያ ኅልውና መጠበቅ ዋስትና እንደሆነ፣ የሁለቱ ጎራ ለይተው መቆም ደግሞ ለኢትዮጵያ መበተን ምክንያት መሆኑን በተጨባጭ እያየን ነው።

ሕዝባችን የትግሬ-ወያኔን ከወጣበት የሥልጣን ማማ ጎትቶ ለማውረድ የአንድነት ድምፁን ከመተማ እስከ ፈርፈር፣ ከዛላንበሳ እስከ ዱፊራ ድምፁን ከፍ አድርጎ በሚጮኽበት፣ ዐማራው በጎበዝ አለቆቹ ፣ኦሮሞው በቄሮዎቹ አማካኝነት የጭቃ እሹህ በሆኑበት ሰዓት፣ ለጉድ የታደለው የግንቦት 7 ከፍተኛ አመራር አባል የሆነው ዶ/ር ታደሰ ብሩ፣«ጮሃ የማታውቅ ወፍ፣ ስትጮህ፣ ጥፉ፣ ጥፉ ትላለች» ዓይነት ንግግር ማድረጉን ከብዙኃን መገናኛ መሣሪያዎች አደምጥን። የንግግሩ ጭብጥ፣ አዲስ አበባ፣የኢትዮጵያውያን ሳትሆን፣ የኦሮሞ ብቸኛ ሀብት ናት፤ ወያኔ የኦሮሞ ነገድ  በአዲስ አበባ ፣ልዩ መብት፣ ጥቅምና መብት አለው  ያለው ትክክል ነው የሚል  ነው። በዚህም ዐማራውም ሆነ ሌሎች ነገዶች በአዲስ አበባ ጉዳይ አያገባቸውም በማለት የብሔርተኝነት አቋሙን በግልጽ ነግሮናል። ይህም የታደሰ ብሩ የግል አቋም ሳይሆን፣ የግንቦት 7 አቋም እንደሆነ ግልጽ ነው። ይህን ከታደሰ ንግግርም ሆነ፣ ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜዎች ስለዐማራና ኢትዮጵያዊነት ካሳየው አቋም በተጨባጭ የታየ ነው።

ከሁሉም በላይ ጥምረት፣ ኅብረት ወዘተ እያለ ከሚጎዳኛቸው ብሔርተኛና ተገንጣይ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጋቸውን ስምምነቶችና ኤርትራ ላይ የመመሸጉን ሁኔታ አጣምረን ስናይ፣ ግንቦት 7 ለዐማራና ለኢትዮጵያዊነት ቀና ራዕይ የሰነቀነው ለማለት ያስቸግራል። መሪው ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የተጓዘበትን የፖለቲካ ሕይወት ስንቃኝ፣ ከመለስ፣ ከታምራት ላይኔና ከበረከት ስምዖን ጋር የነበረውን የጦፈ  በጥቅም ላይ ተመሥርቶ የነበረ ግንኙነት፣ በፕሮፌሰር አሥራት ሕይዎት ላይ ተገንብቶ የነበረው የመላው ዐማራ ሕዝብ አንድነት ድርጅት መሠረት አድርጎ፣ የተደራጀውን የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ድርጅትን ፣ በቅንጅት ስም እንዴት አድርጎ እንዳፈረሰው፤ የቅንጅትን ሕዝባዊ ተቃውሞ ዝግጅቶች እንዴት እንዳከሸፈ ስናጤን፣ የትጥቅ ትግል የሚታሰብ አይደለም ብሎ ያደረጋቸውን ንግግሮች መዝነን፣ እርሱ ወደ ትጥቅ ትግል የገባበትን ሁኔታ ስናስተውል ፣ለዐማራና ለኢትዮጵያዊነት ያለውን የማይናወጥ አቋም በግልጽ እንረዳለን።

እናም በዛሬ ወቅት፣ የሕዝብ አንድነት በሚዘመርበት ሰዓት፣ ታደሰ ብሩ ብቅ ብሎ፣አዲስ አበባ የአንድ ነገድ ብቸኛ ንብረት ናት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ሕዝብ ፍርዱን ይስጥ። እንደ እኛ እምነት ከሆነ፣አባባሉ ከፀረ-ዐማራና ከፀረ-ኢትዮጵያ አቋም የሚመነጭ እና ግንቦት 7 የተቀላቀለውን  የኦፌዴግ ን  አመራር ለማስደሰት ነው ብለን እናምናለን።

ዶ/ር ታደሰ በውስጡ የዲሞክራሲ ጽንሰ ሀሳብ ቢኖር ኖሮ፣ ራሱ በመረጃ የተናገረው፣ ከአዲስ አበባ ነዋሪዎች 56% ዐማራ ነው ያለው፣ ያለማወላወል አዲስ አበባ የዐማራው ናት ባሰኘው ነበር። በዲሞክራሲ ገዥው ሀሳብ፤ የብዙኃን ድምፅ ገዥ ነው የሚለው ነው። በዚህ ከተስማማንና አገሪቱን በነገድ ከከፋፈልን፣ አዲስ አበባ በነዋሪው ቁጥር መብዛት የተነሳ የዐማራው ናት ማለት ነበረበት። ወደ ታሪክም ከሄድን የዛሬዋ አዲስ አበባ የጥንቷ«በረራ» የዐፄ ዳዊት መናገሻ በመሆኗ፣ ያለጥርጥር የዐማራው አጥመ ርስት ናት። ዐማራው የእኔ ብቻናት ሳይል፣ ኢትዮጵያን ለመናድ የፈለጉ አጥፊ ቡድኖች፣ ተረቱን ዕውነት አድርገው ይህ ያንተ ነው፣ ያ ደግሞ የነእገሌ ነው ብለው፣«ውሻ በአጥንት እንደሚጣላ» ሁሉ፣ ጠላቶቻችን በዚህ መሰሎቹ ቅንስናሽ ጥቅሞች እርስ በርሳችን ሊያጠፋፉን ያጠመዱልንን የሤራ ወጥመድ አምኖ፣እነርሱ በከፈቱት ቦይ መፍሰስ፣ ሢሣፋ ፀረ-ኢትዮጵያ፣ ሲጠብ ፀረ-ዐማራ ነውና የዐማራ ድምፅ የሆነው፣ የሞረሽ ወገኔ ዐማራ ድርጅት አባባሉት፣በዝምታ ወይም በቸልታ የማይመለከተው መሆኑን ለወዳጅም ለጠላትም ግልጽ ማድረግ ይሻል። ታሪክ በተደጋጋሚ እንዳሳየን፣ የኢትዮጵያና የዐማራ ጠላቶች ቀድመው ጠፊዎች እንጂ፣ አጥፈተውና ጠፍተው እንኳን የማያውቁ መሆኑን ነውና፣ በማንም ጩኸትና ድንፋታ ዐማራም ሆነ ኢትዮጵያ የማይጠፉ መሆኑን ደጋግመን ልንነግራቸው እንወዳለን!

ድል ለኢትዮጵያዊነት፣

ድል ለዐማራው ሕዝብ!